# ዜና አዲስ ፀረ-ሙስና

ቅጽ 2 ቁጥር 2

የካቲት 2016


## "አስተማሪ ቅጣት የሌላት አገር በምንም አይነት የፀረ-ሙስና ትግሏ ስኬታማ ሊሆን አይችልም፡፡" ከንቲባ አዳነች አቤቤ





የማጠቃለያ ስነ-ሥርዓት

"አስተማሪ ቅጣት የሌላት አገር በምንም አይነት የፀረ-ሙስና ትግሏ ስኬታማ ሊሆን አይችልም።" ሲሉ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አዳነች አቤቤ ገልፀዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን 20ኛውን አለም አቀፍ የፀረ ሙስና ቀን "ሙስና የጋራ ጠላታችን ነው በሕብረት እንታገል!" በሚል መሪ ቃል የማጠቃለያ ስነ-ሥርዓት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህል አደራሽ ህዳር 25/2016 ዓ.ም ተካሂዷል፡፡

በማጠቃለያ መድረኩ ላይ የተገኙት ከንቲባ አዳነች አቤቤ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በከተማ ደረጃ ለመጀመሪያ ጊዜ የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በማቋቋም የፀረ-ሙስና ትግሉን ተቋማዊ አድርጎ ተጨባጭ ስራዎችን በመስራት ላይ ይገኛል ብለዋል። ከንቲባ አዳነች አክለውም ሙስና አገርን ከውስጥ የሚበላ ነቀዝ ነው ያሉ ሲሆን፣ የአንድን አገር እድገት በእጅጉ የሚጎዳ፣ ፍትሃዊ የሀብት ክፍፍል እንዳይኖር የሚያደርግ፣ አገር ገቢዋን በአግባቡ እንዳትሰበስብ የሚያደርግ እና የንግድ ስርዓት በአግባቡ እንዳይከወን የሚያደርግ ለነገ የማይባል እና የሁሉን ርብርብ የሚሻ ጉዳይ ነው ብለዋል።

ወደ ገጽ 3 ዞሯል

## ኮሚሽኑ በመላ ሀገሪቷ ካሉ ኮሚሽኖች 1ኛ በመዉጣት የወርቅ ዋንጫ ተሸላሚ ሆነ፤

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን በመላ ሀገሪቷ ከሚገኙ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የስነ ምግባርና ፀረሙስና ኮሚሽኖች 1ኛ በመዉጣት የወርቅ ዋንጫ ተሸላሚ ሆኗል፡፡

ሽልማቱ በፌደራል ስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን 20ኛዉ የአለምአቀፍ ፀረ ሙስና ቀን አስመልክቶ ባዘጋጀው ሥነ ሥርዓት ላይ የተሰጠ ሲሆን ተቋማት በ2015 በጀት አመት በተሠሩ ሥራዎችና በ20ኛዉ የአለምአቀፍ ፀረ ሙስና ቀን አከባበር ላይ ትግሉን ህዝባዊ መሰረት ለማስያዝ በተደረጉ



በሽልማቱ ወቅት



ወደ ገጽ 6 ዞሯል

ሙስና ስጋት የማይሆንባት አዲስ አበባን እንፈጥራለን!

# ለሙስና አጋላጭ የሆኑ አሰራሮችን መለየትና መፍትሄ መስጠት እንደሚገባ ተጠየቀ፤



የሙስና ተጋላጭነት ጥናት በቀረበበት ወቅት

ኅብረት ሥራ ማኅበራትን ለሙስና ተጋላጭ የሚያደርጉ የሕግ ማዕቀፍ ያልተዘረጋላቸው አሰራሮችን በመፈተሽ የማሻሻያ ሥራዎች ላይ ትኩረት ማድረግ እንደሚገባ ተመላከተ።

የአዲስ አበባ ከተማ ስነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን በኅብረት ሥራ ማኅበራት ላይ ያለውን የሙስና ተጋላጭነትን በሚመለከት ባካሄደው ጥናት ዙሪያ ከዘርፉ ባለድርሻ አካላት ጋር ህዳር 11/2016 ዓ.ም ተወያይቷል።

የአዲስ አበባ ከተማ የስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር አቶ ጀማል ረዲ ኮሚሽኑ በተቋማት ለሙስናና ብልሹ አሰራር ተጋላጭ የሆኑ የአሰራር ስርዓቶችን በጥናት በመለየት የህዝብና የመንግስትን ሀብት ከምዝበራ የማዳን ስራ እየተሰራ ይገኛል ብለዋልን። ኮሚሽኑ በ39 የከተማ አስተዳደሩ ተቋማት የሙስና ተጋላጭነት ጥናት እየተካሄደ እንደሚገኝ ጠቅሰው በሚባክን የህዝብና የመንግስት ሀብት ላይ የአሰራር ሥርዓት በማስተካከል እና የተጠያቂነት ስርዓት ተጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል።

የአዲስ አበባ የንግድ ቢሮ አቶ ቢኒያም ምክሩ የተደረገው የሙስና ተጋላጭነት ጥናት ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ መካሄዱ ተአማኒነት ያለው መሆኑን ገለፀው ለህብረት ስራ ኤጀንሲው ትልቅ ዕድል ነው ብለዋል። አክለውም ኤጀንሲው ከጀመረው የተቋም ማሻሻያ ስራ ላይ በጥናቱ የተሰጡትን ምክረ ሃሳቦች እንደ ግብዓት በመጠቀም የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ማሳደግ እንደሚገባ አመላክተዋል።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ህብረት ስራ ማህበራት ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር ወ/ሮ ልዕልቲ ግደይ በበኩላቸው በተቋሙ የአሰራር ስርዓት ላይ የተጠናው ጥናት የአሰራር ስርዓታችንን እንድንፈተሽ የሚያደርገን ሲሆን ከችግሩ ተስፈንጥረን ለመውጣት ጥናቱን እንደመነሻ መጠቀም እንደሚገባ አመላክተዋል።

የተቀናጀ ሥራ መሥራት ይገባዋል፡፡ ከጎን ሆነው ለማገዝ ዝግጁ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ የስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ም/ኮሚሽነር አቶ አሰግደው ኃ/ጊዮርጊስ እንደተናገሩት የጥናቱ ዓላማ የተቋማትን የሙስና ተጋላጭነትን በጥናት በመለየት ውጤታማ ምክረ ሀሳቦችን ለማመላከት መሆኑ ገልፀው በተቋማት ለሙስናና ብልሹ አሰራር የሚዳርጉ ተግባራትና መንስኤዎቻቸውን በመለየት ቅድመ መከላከል ስራዎችን ኮሚሽኑ ትኩረት ሰጥቶ የሚሰራ መሆኑን አብራርተዋል።

ወደ ገጽ 6 ዞሯል

## ማውጫ


1. ለሙስና አጋላጭ የሆኑ አሰራሮችን መለየትና......... 2
2. ፖሊስ የሙያ ስነ ምግባርን በመላበስ ሙስናን......... 3
3. ተማሪዎች በትምህርት ውጤታቸው ብቻ ሳይሆን ....... 4
4. የሃይማኖት አባቶች አርአያ መሆን........... 5
5. የታማኝነት እሴቶችን በማዳበር ............. 5
6. በ6 ወራት ከ876 ሚሊየን ብር በላይ የህዝብ ሀብት ... 7



በስነ ምግባር ሚዲያና ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት የተዘጋጀ

አድራሻ
በአራዳ ክ/ከ ወረዳ 1 ቸርችል ጎዳና ትንሳኤ ህንፃ 4ተኛ ፎቅ

ጥቆማ ለመስጠት
የነፃ ስልክ መስመር
8887
እንዲሁም በመስመር ስልክ
011 126 61 87
011 126 61 72

Addis Ababa Ethics and Anti-Corruption -ፀረ ሙስና
Addis Ababa Ethics Media
aanticoruption@gmail.co

# ፖሊስ የሙያ ስነ ምግባርን በመላበስ ሙስናን በመከላከል ለሌላው አርአያ እንዲሆን ተጠየቀ፤



የስልጠና ተሳታፊዎች በከፊል

ፖሊስ የሙያ ስነ ምግባርን በመላበስ ሙስናና ብልሹ አሰራርን በመከላከል ረገድ ለሌላው አርአያ መሆን እንዳለበት ተገለፀ።

የአዲስ አበባ ከተማ ስነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ሙያዊ ስነ ምግባርን በመላበስና ሙስናን በመከላከል ረገድ የመርማሪ ፖሊሶች ሚና በሚል ርዕስ ለከተማው መርማሪ ፖሊስ አባላት ስልጠና ጥር 09/2016 ዓም ሰጥቷል።

የአዲስ አበባ ፖሊስ አካዳሚ የስልጠና ዘርፍ ሀላፊ የሆኑት ኮማንደር ጉማታው ገዳሙ እንደገለፁት ስነ ምግባር ከፖሊስ ሙያ ጋር የተቀናጀ መሆኑን አስታውሰው አባላት ሙያቸውን በማክበር፤ በስነምግባር አርአያ በመሆንና በአገልጋይነት መንፈስ ሀላፊነታቸውን መወጣት ይጠበቅባቸዋል ብለዋል። አክለውም ፖሊስ ሙስናንና ብልሹ አሰራርን በመከላከል ረገድ ሚናው ከፍተኛ መሆኑን ገልፀው ከኮሚሽኑ ጋር በቅንጅት መሥራት እንደሚገባ ገልፀዋል፡፡

ስልጠናውን የሰጡት በኮሚሽኑ የስልጠና ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ጀንበሩ ኢርኮ ፖሊስ ሙያዊ ስነምግባርን በመላበስ በህዝብና በመንግስት የተጣለበትን አደራ

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

## "አስተማሪ ቅጣት የሌላት አገር.....

ከገጽ 1 የዞረ

ሙስናን መፀየፍ ላይ እንደበታችን ለግንዛቤ ስራ፣ እጃችን ለንፅህና፣ ሞራላችንም በፍፁም ልዕልና ሊቆም ይገባል ያሉት ከንቲባ አዳነች የከተማችን አመራር የሙስናን ተግባር ለመከላከል የአሰራር ስርዓትን ማዘመን፣ ግልፅነት በተሞላበት ሂደት መስራትና ተቀናጅቶ መታገልን ቅድሚያ ሰጥቶ ሊሰራ እንደሚገባ በአፅንኦት ገልፀዋል።

የአዲስ አበባ ስነምግባር ፀረ ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር አቶ ጀማል ረዲ በበኩላቸው የዘንድሮ 20ኛው የፀረ ሙስና ቀን ስናከብር በከተማ አስተዳደሩ በፀረ ሙስና ትግሉ ያሉ መሻሻሎችን በማስቀጠል እና አመራሩና ባለድርሻ አካላት ሚናቸውን እንዲወጡ በማነሳሳት እንደሆነ ተናግረዉ በዚሁ መሠረትም የፀረ ሙስና ትግሉ ህዝባዊ መሠረት እንዲኖረው በርካታ ስራዎች መሰራታቸውን ጠቅሰዋል፡፡

ሙስና ባደጉትም ሆነ ባላደጉት ሀገራት የሰላምና የልማት ፈተና መሆኑን የውይይት መነሻ ሰነድ ያቀረቡት የኮሚሽኑ ም/ኮሚሽነር አሰፋ ቶላ በመድረኩ ላይ አመላክተዋል፡፡ የሙስና መንስዔ



የማጠቃለያ መድረኩ ተሳታፊዎች

የስነ ምግባር ዝቅጠት መሆኑን ያነሱት ም/ኮሚሽነሩ ኮሚሽኑ በቀዳሚነት ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት በርካታ የስነ ምግባር ግንባታ ሥራዎችን እየሰራ እንደሚገኝ አብራርተዋል፡፡
አያይዘውም ከስነምግባር ግንባታው ጎን ለጎን የሙስና መከላከል ሥራዎች በመሰራታቸው አበረታች ውጤት መገኘቱን ጠቁመዋል፡፡
በመድረኩ በየደረጃው የሚገኙ አመራሮች፣ የሃይማኖት አባቶች፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ አባገዳዎችና ጥሪ የተደረጋለው እንግዶች የተሳተፉ ሲሆን የጋራ ጠላት የሆነውን ሙስና ለመከላከል ከኮሚሽኑ ጋር በጋራ መስራት እንደሚገባ አመላክተዋል፡፡

# ተማሪዎች በትምህርት ውጤታቸው ብቻ ሳይሆን በስነ ምግባራቸውም አርአያ መሆን እንዳለባቸው ተገለፀ፤



የኮሚሽኑና የት/ቢሮ አመራሮች ዕውቅና ከተሰጣቸው ተማሪዎች ጋር

ኮሚሽኑ በስነ ምግባራቸው ተምሳሌት በመሆን ውጤታማ ለሆኑ ተማሪዎች የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ባሉበት የእውቅናና ሽልማት መርሃ ግብር ጥር 25/2016 ዓ.ም አካሄደ ፡፡

በእውቅናና ሽልማት መርሃ ግብሩ ላይ የተገኙት የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት የሰላም፣ ፍትህ እና መልካም አስተዳደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ አቶ ሙሉነህ ደሳለኝ የትምህርት ጥራትን ማረጋገጥ የሚቻለው በስነ ምግባራቸው ምስጉን የሆኑ ተማሪዎችን ማፍራት ሲቻል መሆኑን ገልፀዋል፡፡ አክለውም ስነ ምግባር የሁሉም ነገር መለኪያ በመሆኑ ኮሚሽኑ በትምህርት ተቋማት ላይ እየሰራ ያለው ተግባር የሚበረታታ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ስነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ጀማል ረዲ ተማሪዎች በትምህርታቸው ውጤታማና በስነ ምግባራቸው አርአያ መሆን ይኖርባቸዋል ሲሉ ገልፀዋል፡፡ ከማህበረሰቡ እሴቶች ውጭ የሆኑ መጥፎ



ኮሚሽነር ጀማል ረዲ የቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ አቶ ሙሉነህ ደሳለኝ ሽልማት ሲሰጡ

ባህሪያትን ባለመከተል ሌብነትንና ብልሹ አሰራሮችን የሚፀየፍ ማህበረሰብ ለመፍጠር ሁሉም የድርሻውን ሊወጣ እንደሚገባ ኮሚሽነሩ አሳስበዋል፡፡

አለም አቀፍ ተወዳዳሪ፣ የነቃና የበቃ ትውልድ ለመገንባት ተማሪዎችን በስነ ምግባራቸው አርአያ እንዲሆኑ መስራት እንደሚያስፈልግ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትምህርት ቢሮ ኃላፊ ዘላለም ሙላቱ ዶ/ር ተናግረዋል፡፡ ተማሪዎችን በመልካም ስነ ምግባር ለመገንባትና ለሌሎች ተምሳሌት እንዲሆኑ ለማድረግ ኮሚሽኑ የማበረታቻ ሽልማት መስጠቱ እጅግ የሚያስመሰግን ተግባር በመሆኑ ተጠናክሮ እንዲቀጥል የቢሮ ኃላፊው ገልፀዋል፡፡

የኮሚሽኑ ም/ኮሚሽነር አቶ አሰፋ ቶላ በበኩላቸው በስነ ምግባራቸው የታነፁ ተማሪዎችን ስናመሰግን የታማኝነትና የስነ ምግባር ባህልን ለማዳበር ኮሚሽኑ ያለውን ቁርጠኝነት የሚያሳይ መሆኑን ገልፀው ዛሬ የተመሰገኑ ተማሪዎች ሽልማት ተቀባይ ብቻ ሳይሆኑ ለሌሎች ተማሪዎችም መነሳሳትን የሚፈጥሩ ናቸው ብለዋል፡፡ ሙስናን ለመዋጋትና ፍትሃዊ የሆነ ማህበረሰብ ለመገንባት የሚያስችል ጥንካሬና ድፍረት ያላቸው በስነ ምግባራቸው የተሻሉ ተማሪዎች ሁልጊዜ ሊከበሩ ይገባል ሲሉ ም/ኮሚሽነሩ ጠቁመዋል፡፡

እውቅናና ሽልማት የተበረከተላቸው ተማሪዎችም ለዚህ እድል በመመረጣቸው ኮሚሽኑን አመስግነው በቀጣይም ምስጉን የሆኑ ተማሪዎችን ለማበራከት በሚሰሩ ስራዎች ሚናቸውን እንደሚወጡ ተናግረዋል፡፡

# የሃይማኖት አባቶች አርአያ መሆን እንዳለባቸው ተገለፀ፤





የውይይቱ ተሳታፊዎች በከፊል

የአዲስ አበባ ስነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ከአዲስ አበባ የሃይማኖት ተቋማት ጉባዔ መሪዎች፣ የሃይማኖት አባቶችና መምህራን ጋር በሃይማኖት ተቋማት ውስጥ በሚስተዋሉ ችግሮችና መፍትሔዎቻቸው ላይ የምክክር መድረክ ጥር 28 ቀን 2016 ዓ.ም አካሂዷል።

በምክክር መድረኩ ላይ የአዲስ አበባ ስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ጀማል ረዲ እንደገለፁት ሀገራችን ኢትዮጵያ የአማኞች ሀገር በመሆኗ የሃይማኖት ተቋማት፣ አባቶችና መምህራን የሚያስተምሩት አስተምህሮ ታማኝነትን፣ ርህራሄን፣ ትዕግስትን፣ አብሮነትን፣ ደግነትን እና ይቅርታን የተላበሰ መሆን አለበት ብለዋል። የሙስናና ብልሹ አሰራር ችግሮች መነሻቸው የአስተሳሰብ ጉደለት ነው ያሉት ኮሚሽነሩ የሃይማኖት አባቶች እሴቶች ለማስረፅ ጠንካራ ስራ መስራት አለባቸው ብለዋል።

የኮሚሽኑ ምክትል ኮሚሽነር አሰፋ ቶላ በበኩላቸው የሃይማኖት ተቋማት ማህበራዊ ትስስርን፣ አብሮነትንና በጎነትን የሚያጠናክሩ እሴቶችን የሚሰብኩ መሆን አለባቸው ብለዋል። ማህበረሰቡ ጠንካራ የስነ ምግባር እሴቶች እንዲላበስና ፈታኝ በሆኑ ሁኔታዎች ውስጥ ጭምር ስነ ምግባራዊና ከጥላቻ የራቁ ንግግሮችን እንዲያደርጉ እና መልካም ውሳኔዎችን እንዲወስኑ የሚያስችሉ መሆን አለባቸው ያሉት ምክትል ኮሚሽነሩ በስነ ምግባራቸው ተምሳሌት የሆኑ የሃይማኖት አባቶችና መምህራን በመልካም

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

# የታማኝነት እሴቶችን በማዳበር የትውልድ ስነ ምግባርን መገንባት እንደሚገባ ምሁራን ገለፁ፤



የታማኝነት እሴቶችን በማዳበር የትውልድ ስነ ምግባርን መገንባት እንደሚገባ ኮሚሽኑ ባዘጋጀው ፓናል ውይይቱ የተሳተፉ ምሁራን ገለፁ፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ የስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ከአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ጋር በመተባበር "የሚታመንና የሚተማመን ትውልድ ለመፍጠር የምሁራን ሚና" በሚል መሪ ቃል ከምሁራን ጋር የፓናል ውይይት አካሂዷል፡፡ ለሙስናና ብልሹ አሰራር መከሰት የታማኝነት እሴቶች መዳደል በምክንያትነት ይጠቀሳልና መንስኤው ምን እንደሆነ ያብራሩት በፓናል ውይይቱ የተሳተፉትና ለረጅም አመታት በትምህርት ስራ ላይ የቆዩት ደሞዝ አድማሱ ዶ/ር የሰው ልጅ ፍላጎቶች እያደገ መምጣትና ከሚገባው በላይ በመፈለግ ከስነ ምግባር እሴቶች ያፈነገጠ ተግባር ውስጥ መግባቱ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡ በአሁኑ ጊዜ ጎልቶ የሚታየው

ወደ ገጽ 6 ዞሯል

## ኮሚሽኑ በመላ ሀገሪቷ ካሉ ኮሚሽኖች 1ኛ በመዉጣት......

ከገጽ 1 የዞረ



አቶ አለማየሁ እጅጉ ዕውቅና በሰጡበት ወቅት

ዘረፈ ብዙ ንቅናቄዎች አዲስ አበባ ስነ ምግባርና ፀረሙስና ኮሚሽን የላቀ አፈፃፀም በማስመዝገቡ ተሸላሚ ሆኗል። በሽልማቱ በመላዉ ኢትዮጵያ ያሉ ኮሚሽኖች በ2015 በጀት አመት ያላቸዉ የላቀ አፈፃፀም እንደ አንድ መስፈርት የታየ ሲሆን በተለይ በስነምግባር ግንባታ ስራዎች፣ በአስቸኳይ ሙስና መከላከል፣ በተቋም ግንባታ ስራዎች፣ በሀብት ምዝገባና ማጣራት ስራዎች ባላቸዉ አፈፃፀም መሆኑም በመድረኩ ተመላክቷል።

በተያያዘም ኮሚሽኑ በሀገር አቀፍ ደረጃ ያገኘው ሽልማት ለቀጣይ ስራው መነሳሻ አድርጎ ሊጠቀምበት እንደሚገባ ተገለፀ።

የአዲስ አበባ ከተማ ስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን 20 ኛውን የአለም አቀፍ ቀን ክብረ በዓል የንቅናቄ ስራ አስመልክቶ የላቀ አስተዋጽኦ ላበረከቱ ሴክተር መስሪያ ቤቶችና ክፍለ ከተሞች የእውቅና አሰጣጥ ስነስርዓት አካሂዷል።

በእውቅና አሰጣጥ ስነስርዓቱ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አማካሪና የፖለቲካ ዘርፍ ኃላፊ አቶ አለማየሁ እጅጉ ኮሚሽኑ በሀገር አቀፍ ደረጃ ያገኘው ሽልማት አድንቀው በቀጣይ ኮሚሽኑ በከተማዋ ውስጥ የተንሰራፋውን ሙስናንና ብልሹ አሰራር በመታገል ረገድ ትልቅ ስራ ይጠብቀዋል ብለዋል።

የእኛ ትልቁ ሽልማት ህዝቡ በአገልግሎታችን ረክቶ መመስከር ሲጀምር ነው ያሉት ኃላፊው በዚህ ረገድ የከተማ አስተዳደሩ የአገልግሎት አሰጣጥን በቴክኖሎጂ በመደገፍ ከሌብነትና ብልሹ አሰራር የፀዳ ሥራ መስራት እና እንግልትን የሚቀንስ ቀልጣፋ ለማድረግ እየተሰራ ያለው ተግባር ተጠናክረው ይቀጥላሉ ብለዋል።

## የታማኝነት እሴቶችን በማዳበር....

ከገጽ 5 የዞረ

የግለኝነት ስሜትና አስተሳሰብ በህብረት የመኖር ባህልን በመሸርሸሩ ለታማኝነት እሴቶች መዳደል ዋነኛ መንስኤ መሆኑን ደግሞ በፓናል ውይይቱ የተሳተፉትና በአረማያ ዩኒቨርሲቲ የስነ ልቦና መምህር የሆኑት ገለታ ስጦታ ዶ/ር ተናግረዋል።

የትውልድ ስነ ምግባር መዳደል እንደ ሀገር የሚያሳጣው ነገር ምን እንደ ሆነ የተጠየቁት ገለታ ስጦታ ዶ/ር የትውልድ ግንባታ ስራ በቤተሰብ፣ በመምህራን፣ በትምህርት ቤትና በማህበረሰብ በሚገባ ካልተሰራ ውጤቱ ሀገርን እንደሚጎዳ ጠቁመዋል። በሌላ በኩል ደግሞ በህብረትና በመተጋገዝ ሰርተን ለሀገር ከምናመጣው ሁለንተናዊ ዕድገት ይልቅ እርስ በርስ የመገፋፋት ችግር ውስጥ እንደሚከት ደሞዝ አድማሱ ዶ/ር አስረድተዋል።

ማህበረሰቡ የእኛ ብቻ የሆኑ እንደ ግጭት አፈታት ስርአት ያሉ ሀገር በቀል እሴቶችን በማዳበርና ከውጭ የሚገቡትን በመከላከል በትውልድ ስነ ምግባር ግንባታ ላይ ለውጥ ማምጣት እንደሚቻል ደሞዝ አድማሱ ዶ/ር ጠቅሰዋል።

ትውልዱ ሀገራዊ የሆኑ የታማኝነት እሴቶችን እንዲያጠናክርና ኬሌሎች ሀገራት የወሰዳቸውን ተገቢ ያልሆኑ ባህሎችን እንዲከላከል የማህበረሰቡን የስነ ልቦና ከፍታ ማሳደግ ላይ መስራት ተገቢ መሆኑን የአረማያ ዩኒቨርሲቲ ምሁሩ ገለታ አስረድተዋል።

የሚታመንና የሚተማመን ትውልድ ለመፍጠር ያለው ኃላፊነት ቢለያይም ቤተሰብ፣ መምህራን፣ ትምህርት ቤቶች፣ ማህበረሰቡና የሀይማኖት ተቋማት ስነ ምግባርን በማስረጽና በመገንባት የማይተካ ሚናቸውን ሊወጡ እንደሚገባ ምሁራኑ አሳስበዋል።

## ለሙስና አጋላጭ የሆኑ አሰራሮችን....

ከገጽ 2 የዞረ

በኮሚሽኑ የአስቸኳይ ሙስና መከላከል ቡድን መሪ አቶ ጥላሁን ብርሃኔ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ህብረት ስራ ማህበራት ኤጀንሲ ላይ የተጠናውን የሙስና ተጋላጭነት ባቀረቡት የጥናት ሰነድ ጥናቱ ከማዕከል እስከ ወረዳ የሚገኙ የኅብረት ሥራ ሴክተሮችን ጨምሮ በሥራቸው ያሉ የኅብረት ሥራ ማኅበራትን የሚያካትት መሆኑን አስረድተዋል።

የተቋሙን አሰራር መዳሰስ፣ የሙስና ተጋላጭነትና መንስዔዎችን መለየትና ተጠያቂነትን ማስፈን የጥናቱ የትኩረት አቅጣጫዎች መሆናቸውን ጠቁመዋል።

በመሆኑም ኤጀንሲው በኅብረት ሥራ ማኅበራት የሚስተዋሉ የሙስናና ብልሹ አሰራሮችን ለመለየት የሚያስችሉ ስትራቴጂዎችን በመንደፍ በኅብረት ሥራ ማኅበራት የሕግ ማዕቀፍ ያልተዘረጋላቸው አሰራሮችን በመፈተሽ የማሻሻያ ሥራዎች ማከናወንና የሙስና ተጋላጭነትን መቀነስ እንደሚገባ ምክረ ኃሳብ ሰጥተዋል።

# በ6 ወራት ከ876 ሚሊየን ብር በላይ የህዝብ ሀብት ከምዝበራ ማዳኑን ኮሚሽኑ አስታወቀ፤



የአዲስ አበባ ከተማ ስነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን በ2016 በጀት አመት የመጀመሪያ 6 ወራት የዕቅድ አፈፃፀም ላይ ውይይት ጥር 17/2016 ዓ.ም አካሂዷል።

በውይይቱ ላይ የአዲስ አበባ ስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ጀማል ረዲ እንደገለፁት ባለፉት ስድስት ወራት የተከናወኑ ተግባራት ውጤታማ መሆኑን ገልፀው ቅንጅታዊ አሰራርን በማሳደግ ከማዕከል እስከ ወረዳ የተናበበ ሥራ መሥራት እንደሚገባ ገልፀው ኮሚሽኑ በስነ ምግባር ግንባታና በሙስና መከላከል ላይ አተኩሮ የሚሰራ መሆኑንም አመላክተዋል፡፡

የኮሚሽኑ ምክትል ኮሚሽነር አሰፋ ቶላ በበኩላቸው ኮሚሽኑ በሥነምግባር ግንባታና በሙስና መከላከል ዙሪያ በአጭር ጊዜ የተሰሩ ስራዎች ተስፋ ሰጪ ውጤቶች መመዝገቡን ተናግረዋል፡፡ አክለውም የኮሚሽኑ ሠራተኞች ገለልተኛ ነፃና በእውቀት ላይ ተመስርተው ሥራቸውን ሊያከናውኑ እንደሚገባ አሳስበዋል፡፡

በሀብት ምዝገባና ማሳወቅ ላይ ትልቅ ሥራ መሠራቱን የገለፁት ደግሞ የኮሚሽኑ ምክትል ኮሚሽነር አስግደው ኃይለ ጊዮርጊስ ሲሆኑ ሃብታቸውን ባላስመዘገቡ አመራሮችና ሠራተኞች በቅጣት ጭምር እንዲያስመዘግቡ መደረጉን የኮሚሽኑን የማስፈፀም አቅም ያሳየ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ አያይዘውም ኮሚሽኑ በግማሽ ዓመት 39 ተቋማት የሙስና ተጋላጭነት ጥናት በማጠናት ለተቋማቱ ምክረ ሀሳብ ጭምር ማቅረቡን አመላክተዋል፡፡

ኮሚሽኑ በ2016 የመጀመሪያ ስድስት ወራት ያከናወናቸው ዋና ዋና ተግባራት ለ910,350 ከማህበረሰቡ ለተውጣጡ አካላት እና ለ162,450 አመራርና ሰራተኞች የግንዛቤ ማስጨበጫና የአቅም ግንባታ ስልጠና መስጠቱ ተመላክቷል፡፡ በ253 የመንግስት የመጀመሪያ ደረጃ እና 78 የ 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች በድምሩ 331 ክበባት ማቋቋሙን ኮሚሽኑ አሳውቋል፡፡

በሌላ በኩል 8,409 የከተማው አመራሮችና ሠራተኞች ሀብት ማስመዝገባቸው በሪፖርቱ ተገልጿል፡፡ ለኮሚሽኑ ከደረሱ 792 ጥቆማዎች ዉስጥ የተጠና 592 እና አግባብነት የሌለዉ 21 ሲሆን ቀሪዎቹ 179 በሂደት ላይ ይገኛሉ፡፡ ከምዝበራ የዳነ የመንግስትና የሕዝብ ሀብት በገንዘብ ሲተመን በመደበኛ 534,455,404.00 ብር እና በአስቸኳይ መከላከል 342,450,378.67 ብር በአጠቃላይ 876,905,782.67 ብር ማዳን የተቻለ ሲሆን በአይነት 171 ጠቅላላ ንብረት እና 14684.5 ካሬ ሜትር መሬት ማዳን መቻሉን በሪፖርቱ ላይ ተመላክቷል፡፡

## የሃይማኖት አባቶች አርአያ መሆን....

ከገጽ 5 የዞረ

ባህሪ የታነፀ ትውልድ ለመፍጠር ያላቸው ሚና የላቀ መሆኑን አመላክተዋል።

በውይይቱ ላይ የተሳተፉ የሃይማኖት አባቶችና መምህራን በስነ ምግባር የታነፀና ሙስናን የሚፀየፍ ትውልድ ለመገንባት በሚደረገው ጥረት ሚናቸውን እንደሚወጡ ገልፀዋል። አክለውም መንግስት ለሌብነትና ብልሹ አሰራር በር የሚከፍቱ አሰራሮችን ተከታትሎ በማረም እና ተጠያቂነትን በማጠናከር የድርሻውን እንዲወጣ ጠይቀዋል።

"የሃይማኖት ተቋማት መልካም ባህሪ ያለውና ሙስና የሚፀየፍ ትውልድ ከመገንባት አንፃር ያላቸው ሚና" የሚል የመወያያ ሰነድ በኮሚሽኑ የስልጠና ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ጀንበሩ ኢርኮ ቀርቦ ውይይት ተካሂዶበታል።

## ፖሊስ የሙያ ስነ ምግባርን በመላበስ ....

ከገጽ 3 የዞረ

መወጣት እንደሚገባው ተናግረዋል። አያይዘውም ፖሊስ የህግ የበላይነት በማከበርና በማስከበር ሙያዊ ግዴታውን መወጣት እና ገለልተኛ ሆኖ ማገልገል ይጠበቅበታል ብለዋል፡፡ በከተማችን የሚስተዋሉ የፀረ ሙስና ትግሎች ላይ ሙያዊ ስነ ምግባር በተላበሰ መልኩ ተገቢውን ሚና ሊወጡ እንደሚገባ ዳይሬክተሩ በስልጠናው ላይ አብራርተዋል።

ሙያዊ ስነምግባር የተላበሰ የመርማሪ ፖሊስ አባላት የተሰጠውን አደራና ሀላፊነት በብቃት ለመወጣት የሚያስችል በሙያ ነፃነት፣ ከአድሎአዊነት የፀዳ ስራ መስራት፣ የሙያ ብቃትና ትጋት፣ ኃላፊነትና ተጠያቂነት ቅንነት ሃቀኝነት ታማኝነት፣ የሰብዓዊ መብቶችን ማክበር፣ የማህበረሰብ ተጠያቂነትን ማሳደግ፣ የስነ ምግባር አመራር መስጠት እሴቶችን እንዲያዳብሩ የሚያደርግ ነው፡፡

በስልጠናው ላይ የተሳተፉ የፖሊስ አባላት በህዝብና በመንግስት የተሰጣቸውን አደራና ሀላፊነት በብቃት ለመወጣት እንደሚሰሩ ገልፀው የተሰጣቸው ስልጠና ግንዛቤ ከማስጨበጡ በተጨማሪ ተነሳሽነት እንደፈጠረላቸው ሀሳባቸውን ገልፀዋል።

# የአዲስ አበባ ከተማ ስነ ምግባርና ፀረሙስና ኮሚሽን

## ፎቶ ቅኝት













አድራሻ:- በአራዳ ክ/ከ ወረዳ 1 ቸርችል ጎዳና ትንሳኤ ህንፃ 4ተኛ ፎቅ ጥቆማ ለመስጠት የነፃ ስልክ መስመር 8887
እንዲሁም በመስመር ስልክ 011 126 61 87 እና 011 126 61 72

በስነምግባር ሚዲያና ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት የተዘጋጀ